# ይድረስ ለኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ

**ባሉበት**

15 January 2018
Germany

ያልተገራ ፈረስ ደርጉ እያላችሁ
ፈርጥጦ ፈርጥጦ ገደል ገባላችሁ ........... የሚለው የ1966ቱ የለውጥ ማግስት የወቅቱ ወጣቶች ዜማወግ ሰሞኑን ትዝ ትዝ እያለኝ ነው ፡
መንግሥት ግራ እንደገባው የተረዳው የያኔው ተማሪዎች መካከል እርስዎም የወቅቱ ወጣት ነበሩና መዝሙሯን በደንብ እንደሚያስታውሷት አልጠራጠርም።
በሃገሩ ፖለቲካና በኑሮው ብሶት የተወለደው የህዝብ ቁጣ ባመጣባችሁ ከባድ የፖለቲካ ማዕበል የተነሳ ብዙ ቀናትና ለሊቶችን በዝግ አዳራሽ ተወጥራችሁ ስታምጡ ቆይታችሁ ተገላገልን ያላችሁትን መፍትሄ እርስዎ ሊነግሩን በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው በአማርኛ ቋንቋ ለሃገራችን ህዝብ የተናገሩትን 100 ሚሊዮን ህዝብ በጥንቃቄ ነበር ያዳመጠዎት ፤
" ሃገራዊ መግባባት ተግዳሮትን ከፍ ለማድረግ ሲባል በክስ ላይ ያሉ ክሳቸው ተቋርጦ ፡ በምርመራም ላይ ያሉም ምርመራቸው ተቋርጦ ፡ እንዲፈቱ ይደረጋል " ብለውናል።
ልጠይቅዎ ... እስረኛን ክስ አቋርጦ ለመፍታት ስንት ጊዜ ይፈጃል ? ከዚህ አባባልዎ የተረዳነው የ 5 አመት የመንግስትዎ እቅድ ሊፈጅ የሚችለው 25 አመት መሆኑን ነው ምክንያቱም የተ ቋረጠው የፖለቲካ እስረኞች ክስ ሳይሆን የእናንተ ውሳኔ ነው ። ለመሆኑ ስንት ዓመት ነው በስልጣን ላይ መቆየት የምትፈልጉት ? እባክዎ ይመልሱልኝ።
ይህ ለመላው ኢትዮጵያዊ የተለመደ ሃዘን ከመፍጠሩ በስተቀር እጅግም አያስገርምም ምክንያቱም የተለመደ ጉዳይ ሆኗል።
በጣም ያስገረመኝ እና ይህንን ደብዳቤ እንድጽፍልዎ ያነሳሳኝ ከዚያ ቀጥሎ ባደረጉት ንግግር የጎሳ የበላይነት በሃገራችን ውስጥ ጨርሶ የለም ማለትዎ ነው።
እንደምን አደሩ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ?
በሃይማኖት ሥርዓት ተቀርጸው እንዳደጉ፡ በአዲስ አበባም ሆነ በአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች የተማሩ ስለመሆንዎ ፡እናውቃለን ( ዳሩ የፖለቲካ ሆነ የሃይማኖት መሪዎች መች ውነት ይናገራሉ )
የማልደብቅዎ ነገር ቢኖር የአንድ ጎሳ የበላይነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሲያስረዱ የተናገሩትን በደንብ ካዳመጠ በኋላ ህዝቡ በሃዘን ስቆብዎታል ፡
ምክንያቱም በትግርኛ የተጻፈውን የጎሳ ፖለቲካ ሃሳብ ወደ አማርኛው መልሶ ማቅረብ ተስኖዎት እንደሆነ ስለተረዳ ። ምነው በሚችሉት ቋንቋ ቢናገሩ ? ነበር የተባሉት።
ይህ አባባልዎ አንድ ነገርና አንድን ወቅት አስታወሰኝ ፤ ኮሎኔል መንግሥቱ ሃይለማርያም በሽሽታቸው መባቻ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባደረጉት ረዥምና አሰልቺ ንግግር ላይ ((( እውን ደርግ አለ ))) ሲሉ መደመጣቸው ትዝ አለኝ ።
ዛሬም እርስዎ ከ27 አመታት በኋላ እውን የዘር የበላይነት አለ ? ማለትዎ የጊዜያቶችን መመሳሰል የሚያረጋግጥ ይሆን ? ይህች የቤተመንግሥት የስንብት ንግግር እንደሆነች ባስብም የኮሎኔል መንግሥቱን እድል ማግኘት ዛሬ የማይታሰብ መስሎ ይታየኛልና እርስዎም ይታይዎት ለማለት ፈልጌ ነው::
በመሠረቱ ህወሃት የፖለቲካ ፓርቲ ይሁን የንግድ ድርጅት የኢትዮጵያ ህዝብ አያውቅም ብለው እንደማይገምቱ አምናለሁ::

ነገር ግን እርስዎ የመጡበት ፓርቲ አባል የሆነ በሃገሪቱ ከፍተኛ የውሳኔ ሰው ፡ወይንም ባለስልጣን፡ አንድ እንኳ ሊነግሩን እያልቻሉ እኩል ነን ማለትዎ ሃቅ መናገርዎ ነው ማለት ነው እንበልና የሃገሪቱ የመከላከያ ቁልፍ ሰዎች፤ የሃገሪቱ የደህንነት ዋናዋና ሰዎች፤ ከከፍተኛ እስከ ትንንሾቹ የንግድና የገቢ ተቋማት ቁልፍ ሰዎች እነማን ናቸው ?
ወሳኝ እና የከፍተኛ የመንግስት አመራር ሰዎች እነማን ናቸው ?
አደራዎን እኔ እንዳይሉኝ .......... እርስዎ ወሳኝ ሰው አይደሉም ይልቁንም ስለ ሃይማኖትዎ ስለ እውነት ብለው አንድ ቀን እውነትን መስክረው መኖር ቢቀርብዎ እንኳን ጽድቅን ይወርሳሉና ወደ ራስዎ ይመለሱ ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፤የንግድና ብሄራዊ ባንኮች ፤የገቢና ወጪ ተቋማት፤ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የመከላከያና  የፖሊስ ሠራዊት ወዘተ ቁልፍ ሰዎች
ባጠቃላይ ጅግ በብዙ ቦታዎች ተሰግስገው ሃገሪቱን በተለይም በንግዱና በፖለቲካው ዘርፍ ሰንገው የያዟት ኸረ በየቀበሌውና በየ ቦታው ሳይቀር ህዝቡን ያለ ጉበ  አላንቀሳቅስ ብለው  ቀስፈው የያዙት እነማን ናቸው ? አደራዎን መልስ እንዳይሰጡኝ ፡ዝም ይበሉ ፡ ምክንያቱም ውነቱን ሊነግሩን አይችሉም እውነቱማ ሁልጊዜም ከህዝብ ጋር አለ::
ስለምን ሊዋሹን እንደፈለጉ ባይገባንም መዋሸት እንዳለብዎ ግን ይገባናል

የትግራይ ህዝብ ለዚህ ላለንበት ታላቅ ድል ስላበቁን ዋጋቸው ገና አልተከፈላቸውም የሚል መልዕክት ያለው ንግግርዎ ደሞ በቁም እንዳለቅስልዎ ነው ያደረገኝ።
ምን ለማለት እንደፈለኩ መቼም ይገባዎታል ፡ አሁን ወደኋላ ተመልሼ የትግራይ ልጆችኮ የታገሉት ለዚህ ለዚህ ነበር ይህን ያደረገው ወቅቱ ነው .. ቤተመንግሥት ሳይሆን መቀሌ ነበር ድንበራቸው .ወዘተ ሁኔታዎችን ላንዱ ክፉ ላንዱ ደሞ ጥሩ ሆኖ ነው ይህ ይሆነው ብዬ የምተነትንበት ምክንያትም ጊዜም ሞራልም የለኝም ፡ ስለዚህ እንዲህ ያለውን አስተሳሰብዎን ደግሜ ብሰማ ወላዲተ አምላክን አንድ ቀን አያድሩም።
ሥራ አመራሮችና መሪዎቻችሁ የምታስተምሯቸው አንድ የንግግር ፈሊጥ አለ " በመሠራት ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው " በመደረግ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው ወዘተ ይህ የፖለቲካ ማደንዘዣ ነው። አሁን አሁንማ ጋዜጠኞች ሌሎችም ሁሉ በማደንዘዣው ቃል ካልተናገራችሁ ወዮላችሁ የተባሉ ይመስል አንድ ጥያቄ የቀረበለት የስራ መሪ ሳይቀር ለምን አልተከናወነም ተብሎ ሲጠየቅ በመከናወን ላይ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ከሚል መልስ በስተቀር ምንም አይገኝም።
እርስዎም እስረኞቹ ለምን አልተፈቱም ቢባሉ የሚመልሱትን አውቃለሁ ( በመፈታት ላይ ያሉበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው) ብለው ይሉናል።
የዛሬ ተቃዋሚ እንደው አፈ ዘራፍ የበዛበት ብቻ ሆኖ ነው እንጂ እንደቀድሞው ቢሆን ኖሮ ወላዲትን እርስዎ እዚያች ወንበር ላይ አይገኙም ነበር።
ዛሬ እኔም ባለሁበት የስደት ሃገር ከወዳጆቼም ከታናናሾቼም የሃገር ጉዳይ ተነስቶ በተጫወትን ቁጥር ረጋ ያለና ሰከን ያለ አስተሳሰብ ያለው ሰው ማግኘት ውድ ሆኗል ። ከጥቂት የቃላት ልውውጥ በኋላ ማን እንደሆንክ ፈርጀህ ዞር ከሚል በስተቀር ገባ ብሎ የሚወያይ እጅግ ጥቂት ነው ፡ ይሄ ደሞ 27 ዓመታት የደከማችሁበት ለእርስዎና ለሚታመኑለት ነገር ግን ህዝብንና ሃገርን ለሚበድል መንግስትዎ ትልቅ ግብዓት ሁኗል ብዬ አምናለሁ።
አሁን በማምላክ በሃገራችን የፖለቲካ እስረኛ የለም ብላችሁ ስትሉ ትንሽ እንኳ አይሰቀጥጣችሁም ? የፖለቲካ እስረኛ ማለት ደሞኮ ምን ማለት እንደሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ልታስረዱ መሞከራችሁ ? ኸረ ጠቅላይ ሚኒስትር ኸረ በፈጠረዎ ስልጣንዎ ጥንቅር ብሎ ይቅር በሞያዎ ተከብረው ይኑሩ ... መልካም ትዳር አለዎት ፤ ልጆች ወልደዋል፤ ምናልባትም የልጅ ልጅ አይተዋል ኑረውና ተምረው ያልጠገቡ ልጆች የባህርን ከርስ እየሞሉ የአረብ መጫወቻ እየሆኑ የተማረው ሃገሩን ትቶ ለሰው ሃገር እያገለገለ ህዝቡ

በርሃብና በኑሮ ውድነት መግቢያ እየጨነቀው ጉበኝነትና የአንድ ጎሳ የበላይነት በሃገሪቱ ጫንቃ ላይ ነግሶ እንዴ ምነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኸረ ስለህሊናዎ ብለው መለስ ይበሉ።
ከውጪ የሚገባ አንድ ዜጋ አንዲት የቤት መጥረጊያ አልያም የእጅ ስልክ እንኳ ይዞ መግባት የማይፈቀድለት በሃገሩ መብት የሌለው ህዝብ እኮ ነው እየመሩ ያሉት ።
ይህ እስከመቼ ነው የሚቀጥለው ? ይብቃዎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

ዘፋኙ ፤ እየነገራችሁ እኮ ነው ፡ደራሲው፣ ገጣሚው፣ ጸሃፊው፣ በጠቅላላ በግልጽም በሚስጥርም መናገር ከጀመረ ሰንብቷልኮ ምነው እንዲህ መስሚያችሁ ጥጥ ሆነሳ ?
ኸረ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ህዝብን ያሸነፉ አንዳችም ነገስታቶች ወይም ባለ ብዙ የጦር ሠራዊት መሪዎች ወይም ደሞ ሃያልና አይበገሬ የተባሉ የሃገርና የፓርቲ መሪዎች ወዘተ ጨርሶ በዚህች ዓለም ላይ አይገኙም ! የሉምም ። እናንተም ወላደተ አምላክ ምስክሬ ናት አታሸንፉም::
የኤርትራ ችግር ሃገሪቱን ወደየት እየወሰዳት እንደሆነ የተረዳችሁ አይመስለኝም የህወሃት መሪዎች የተረዱት ነገር ቢኖር የሃገሪቱን ሃብት ወንዝ ማሻገር ብቻ ነው ።
ይህንንም አስከትሎ በአባይ ግንባታ በኩል እየተከሰተ ያለውን እና የሚያስከትለውን ሁኔታ ከወዲሁ ጠንቀቅ ብላችሁ ያወቃችሁበት አይመስልም
የሶማሊያን እና የደቡብ ሱዳንን የድንበርና አካባቢው ችግር አሁን ባለው አቅም መቋቋም ስለተቻለ ብቻ እንቅልፍ የሚያስተኛ ጸጥታ ነው ብላችሁ የተዋችሁት ይመስላል ዳሩ የውስጥ ችግሩ አላስቆም አላስቀምጥ ብሏችኋል።
ስለዚህ እርስዎም ሆኑ የበላይዎ ወያኔዎች ህዝብን ስሙ !!! ወጣቱን አድምጡት !!! ቄሮን እና ፋኖን ችግራችሁ ምንድነው በሏቸው !!!
ዛሬ ደሞ እንደሰማነው ልንፈታቸው ያዘጋጀናቸው ሰዎች በጸረሽብር ያልተከሰሱ
ህዝብን በማበጣበጥ ያልተወነጀሉ ፤ ምንም ዓይነት ወልጀል ያልተገኘባቸው ወዘተ የሚል ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እነዚህ ሠዎች ምንም ወልጀል ካልሰሩ ቀድሞውንስ ስለምን ታሠሩ ? እባክዎ እግረመንገድዎንም ይህቺን ጥያቄ ሳይመልሱልኝ እንዳይወርዱ ።
እንግዲህ 30 ዓመት ለትዕግስት ብዙ ነውና ልብ ያለው ልብ ይበል ።
መርሕ አልባ ማደንዘዣ ይቁም !!
ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ መርህ አልባ አሠራር ከምኒልክ ቤተመንግሥት መቼና እንዴት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲወጣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንዴ ተነስቶ ባዶ እጁን እንዳይመለስ ሊሆን የቀረዎት አንድ ሃሙስ ብቻ ነውና ወደ ክርስትናዎ ተመልሰው ንስሃ ይግቡ በማለት የዛሬውን መልክቴን እቋጫለሁ።
አክባሪዎ

ገልገሎ ሰሎሞን